ዐይነት ፤	ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ዜና ፡ ስሌት ። "
ርእስ ፤	"ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ። "
ደሁሲ ፤	"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ።
ዕለት ፤	ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ።
ዝግጅት ፤	ፍጹም ።
መጽሔት ፤	"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ቁ.2011-001 ።
ማስታወሻ ፤	
ማሳሰቢያ ፤	

ዜና ፡ ስሌት ።

Computing News | Nouvelles d'informatique

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለው ፡ ነጻ ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መሳሊያ ፡ ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ወጥቷል ፤ ከመርበቢያው ፡ ከ ፦ http://www.awdeqelem.net በነጻ ፡ ይቀዳል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ ክለሳ ፡ 1.0 ፡ መስከረም ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ ሲወጣ ፥ በኢትዮጵያዊ ፡ ስሌት ፡ ታሪክ ፡ የመዝመሪያውን ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፡ (spell-checker | correcteur orthographique) ፡ አበርክቶልን ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፥ አንድያው ፡ ባለፊደል ፡ መጠንቀቂያና ፡ ባለመዝገበ ፡ ቃላት ፡ **መግበር** ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቀጥሏል ።

ይህ ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ የምናወራኘው ፡ ዜና ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ስሌትን ፡ አንድ ፡ ርምጃ ፡ ስላራመደ ፡ መሻሻል ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መግለጫን ፡ እናቀርብበታለን ❖

©አ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።